# ጥናት አንድ ኢዩኤል 1፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እግዚአብሄር በባሪያው በነብዩ ኢዩኤል በኩል ልያስተላልፍ ያለውን መልዕክት እንዲሰሙለት የፈለጋቸው ሰዎች በቁ2 ላይ የሚገኙ ሲሆኑ እነርሱም፤ በአገሪቱ የሚኖሩት ሽማግሌዎችና፤ በምድሪቱ ላይ በሚኖሩት ነዋሪዎች በሙሉ መልዕክቱ መደመጥ እንደሚኖርበት እንረዳለን። ለመልዕክቱ አድማጮች ደግሞ እግዚአብሄር ሲያቀርብላቸው የምናየው ጥያቄ፤ "በእናንተ ዘመን፣ በአባቶቻችሁ ዘመን እንዲህ ዓይነት ነገር ሆኖ ያውቃልን?" የሚል ጥያቄ ነው የቀረበላቸው።
2. ከልጅ ልጅና ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ እግዚአብሄር የፈለገውና እርሱ ራሱ በህዝቡ ላይ ያመጣው አድርጎ የሚናገረው በቁ4 ላይ ተዘርዝሯል፤ ይኸውም ከአንበጣ የተረፈውን ትልቁ አንበጣ እንደበላው፣ ከትልቁ አንበጣ የተረፈውን ኩብኩባ እንደበላው፣ ከኩብኩባ የተረፈውን ደግሞ ሌሎች አንበጦች እንዲበሉት እንደተደረገ ነው የሚነግረን። እነዚህ ከእግዚአብሄር መልዕክት የመጣላቸው ሰዎች በቁ5 ላይ የምናገኛቸው፤ እናንተ ሰካራሞች ተንስታችሁ አልቅሱ የተባሉትና፤ ዋይ እንዲሉ የተነገራቸው የወይን ጠጅ ጠጪዎች ናቸው።
3. በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናነበው አስከፊ ሁኔታ በምድሪቱ ላይ መከሰቱ ከሌላ ቦታ ሁሉ አልፎ በእግዚአብሄር ቤትም ውስጥ እንኳን ችግር እንደፈጠረ ከቁ9 ላይ መረዳት እንችላለን፤ ይኸውም የእህልና የመጠጥ ቁርባን ከእግዚአብሄር ቤት እንደተቋረጠ፣ በእግዚአብሄር ቤት እያገለገሉ ያሉት ካህናትም በዚህ ምክንያት እያለቀሱ እንዳሉ እናያለን። ይህ ሁሉ በምድሪቱ ላይ የተከሰተው ነገር በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ብዙ ሊያስከትል የሚችላቸው ነገሮች እንዳሉ ቢታወቅም እንኳን፤ ዋነኛውና በቁ12 ላይ የተነገረን ግን፤ ከሕዝቡ ህይወት ውስጥ ደስታ እንደራቀ ነው የሚናገረው።
4. ምንም እንኳን ለዚህ ለተፈጠረው ሁኔታ ሁሉ ተጠያቂዎች ናቸው ባይባልም እንኳን፤ እግዚአብሄር በቅድሚያ ንስሃ እንዲገቡ፣ ማቅ እንዲለብሱና፣ እንዲያለቅሱ የሚናገረው በእግዚአብሄር መሰዊያ ላይ በአገልግሎት ላይ ለተሰማሩት ካህናትና፤ በመሰዊያው ላይ ለሚያገለግሉት አገልጋዮቹ ነው። ንስሃውና ለቅሶው በካህናቱ ብቻ የሚያበቃ ነገር እንዳልሆነና ካህናቱ የአገር ሽማግሌዎችን በመሰብሰብ፣ የአገሪቱን ነዋሪዎች ሁሉ ያካተተ የፆምና የእግዚአብሄርን ፊት የመፈለጊያ ጊዜ እንዲያውጁ ማድረግ ተጨማሪ ሃላፊነት ሲሰጣቸው ነው የምንመለከተው።
5. ሃጥያት የህዝብን ደስታና ተድላ እንደሚያራቁትና በቁ12 ላይም ህዝቡን ደስታ ቢስ እንዳደረገው ያነበብንም እንኳን ቢሆን፤ በጣም የሚያሳዝነው ነገር ግን የደስታና የተድላ ምንጭ ሊሆን የሚገባው የእግዚአብሄር ማደሪያ እንኳን በሃጥያት ምክንያት ደስታና ተድላ ጠፍቶበት እንደሚገኝ ቁ16 ግልጽ አድርጎ ሲነግረን፤ ቁጥሩን በትኩረት ብናነበው ተቋረጧል ነው የሚለን፤ ይህ የሚያመለክተው ቀድሞ ደስታና ተድላ የሚፈስበት ቤት እንደነበረና አሁን ግን እንደተቋረጠ ነው።
6. በምድሪቱ ላይ የተከሰተውን የምግብ እጥረት አስመልክቶ እነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናነበው፡- ዘሩ በአፈር ውስጥ በስብሶ እንደቀረ፣ ግምጃ ቤቶቹ እንደፈራረሱ፣ ጎተራዎች እንደተሰባበሩ፣ እህሉ እንደደረቀ፣ መሰማሪያ ስለሌላቸው ከብቶች እንደተደናገጡና መንጎች እንደጮሁ፣ የበግ መንጎችም እንደተቸገሩ፣ መሰማሪያቸውን እሳት እንደበላው፣ የዱር ዛፍ ሁሉ ነበልባል በልቶታል፣ የዱር አራዊት ወደ እግዚአብሄር እንዳለከለኩና ወራጅ ውሃም ሁሉ እንደደረቀ ይነግረናል። ይህንን ሁሉ አስከፊ ነገር እየተናገረ ምናልባትም ነብዩ ኢዩኤል ሳይሆን አይቀርም ስለ አገሩ በቁ19 ላይ መከራውን መናገር አቁሞ ወደ እግዚአብሄር ፀሎት ሲያደርግ ነው የሚታየው።
7. በአብዛኛው የተለመደውና ለልጆቻቸው እንዲያስተላልፉት የሚጠየቁት መልዕክት የእግዚአብሄርን እርዳታና ያደረገላቸውን መልካም ነገር ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው ነገር ግን፤ እግዚአብሄር በሕዝቡ ላይ ያመጣውን መቅሰፍትና ፍርዱን ነው ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሁሉ እንዲተላለፍ ነው በቁ3 ላይ የአገሩን ሽማግሌዎችና በመድሪቱ ውስጥ እየኖሩ ያሉትን ሰዎች ሁሉ እንዲያደርጉት የሚያዘው።

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ (253) 653-4707 

# ጥናት ሁለት ኢዩኤል 2፡1-32 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ነብዩ ኢዩኤል በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሕዝቡን ሲያስጠነቅቅ የምናየው፤ የእግዚአብሄር ቀን እንደቀረበና፣ እርሱም በደጅ እንደሆነ፤ ስለዚህም በምድሪቱ የሚኖሩ ሁሉ እንዲንቀጠቀጡ ነው የሚነግራቸው? እግዚአብሄር በሚያስፈራራና ሕዝቡን በሚያንቀጠቅጥ ዓይነት መልዕክት በተደጋጋሚ ይናገር እንጂ ዓላማው ህዝቡ በሚመጣው ነገር የመፍራትና የመደንገጡ ጉዳይ ሳይሆን፤ ሊመጣ ያለውን አስከፊ ሁኔታ ተረድቶ ሕዝቡ በንስሃ ወደ አምላኩ እንዲመለስ ለማድረግ ነው የእርሱ ዋነኛ ዓላማ።
2. ስለዚህ ቀን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ እንደተነገረ ቢታወቅም፤ በዚህ በቁ2 ውስጥ ግን የተነገሩት ነገሮች፤ በአንደኛ ደረጃ ይህ ቀን የጨለማና የጭጋግ ቀን እንደሆነ ሲናገር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ቀን የደመናና፣ የድቅድቅ ጨለማ ቀን እንደሆነ እናነባለን። ስለሚመጣው ሰራዊት ደግሞ የሚናገራቸው ሁለት ሃሳቦች፤ ይህ ሰራዊት ሃያል ሰራዊት እንደሆነ ሲናገር፤ ሌላው ደግሞ ሰራዊት በቁጥር ሲታይ ደግሞ ብዙ በማለት ነው የሚገልጸው። ይህ ሃያልና ብዙ የሆነው ሰራዊት በፊቱ እሳት ይበላል፣ በኋላው ደግሞ ነበልባል ይለበልባል፤ ሌላው ደግሞ በፊታቸው እንደ ኤደን ገነት የነበረው ነገር፤ ከኋላቸው ወይም አልፈውት ሄደው ሲታይ ልክ እንደ ባዶ ምድረ በዳ አድርገውት ነው እንደሚያልፉ ነው የሚናገረው።
3. ይህ አስፈሪ እንደሆነ የሚነገርለት የጌታ ቀን በመባል የሚታወቀው ቀን አስፈሪነቱ እግዚአብሄርን ለናቁና ከእርሱ ጋራ ያላቸውን ግንኙነት ላላስተካከሉ ሰዎች እንጂ፤ የህይወታቸው እርምጃ ከእርሱ ጋራ ለተስተካከለ ሰዎች ይህ ቀን አስፈሪ ሳይሆን የሚናፍቁት ቀን ሊሆን ይገባል። ኢዩኤል ሙሉ ለሙሉ ቀኑን የሚያቀርበው የሚያስፈራና የፍርድ ቀን እንደሆነ አድርጎ ሲሆን፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ለቆሮንቶስ ቅዱሳን ቀኑን የሚያቀርበው ሊናፍቁት የሚገባ የተቀደሰ ቀን አድርጎ ነው የሚስልላቸው።
4. ስለ እነዚህ ሰራዊት የተነገረ ብዙ ነገር ቢኖርም ቁ8-9 የሚናገሩት ነገር፤ ሰራዊቱ እርስ በእርሳቸው አይገፋፉም፣ እያንዳንዱ መንገዱን ጠብቆ ይሄዳል፣ መስመራቸውን ሳይለቁ መከላከያውን ሰብረው ያልፋሉ፣ ከተማይቱን ይወራሉ፣ በቅጥሩ ላይ ይዘላሉ፣ በቤቶች ላይ ዘለው ይወጣሉ፣ እንደሌባም በመስኮት ይገባሉ። ይህ ታላቅ ሰራዊት እጅግ አስፈሪና ታላቅ፣ በብዛትም ቁጥሩ የበዛ ይሁን እንጂ ትዕዛዝን የሚቀበለ ከእግዚአብሄር አምላክ እንደሆነ ቁ11ድን ስናነብ ግልጽ አድርጎ ይነግረናል።
5. እግዚአብሄር በነብዩ ኢዩኤል አማካኝነት ሕዝቡ በአምላኩ ፊት እውነተኛ የሆነ ንስሃ እንዲገባ በማበረታታት ምህረትን እንደሚቀበሉ እርግጠኛ እንዲሆኑ የሚያቀርብላቸው የእግዚአብሄር ባህርያት በቁ13 አጋማሽ ላይ የምናነባቸው ሲሆኑ እነርሱም፡- "እርሱ መሃሪና ርህሩህ" እንደሆነ፣ "ቁጣው የዘገየና ፍቅሩ የበዛ" አምላክ እንደሆነና፣ ክፉ ነገርንም ከማምጣት የሚታገስ" መሆኑንም በማስታወስ ነው። ለንስሃ የሚደረገው ጥሪ ከሚያካትታቸው ሰዎች መሃል የሚገኙት፤ ሽማግሌዎች፣ ሕጻናት፣ ጡት የሚጠቡት፣ ሙሽራው፣ ሙሽሪት፣ ካህናቱና ሕዝቡ በሙሉ ይገኙበታል።
6. የንስሃ ፍሬ ከሆኑት መሃል፡- እህል፣ የወይን ጠጅና ዘይት እስኪጠግቡ ድረስ ማግኘት(ቁ19)፣ እንደቀድሞው የበልግንና የጸደይን ዝናብ በብዛት ማግኘት(ቁ23)፣ የአውድማዎች በእህል መሞላት(ቁ24)፣ በአንበጣ የተበሉት ዓመታት መመለስ(ቁ25)፣ እስኪጠግቡ ድረስ የሚመገቡት ምግብን ማግኘት(ቁ26)፣ ሕዝቡ ከእንግዲህ ወዲህ አያፍርም(ቁ27)። በምዕራፍ አንድ ውስጥ፤ ሕዝቡ በሃጥያታቸውና ከእግዚአብሄር ጋራ የነበራቸው ግንኙነት በመበላሸቱ ምክንያት ከውስጣቸው ደስታና ሃሴት እንደጠፋባቸው ስንመለከት፤ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ደግሞ፤ ከልብ የሆነና እውነተኛ ንስሃ ሲገቡ ያ ከልባቸው የጠፋው ደስታና ሃሴት እንደተመለሰላቸው ነው እንግማራለን።
7. ኢዩኤል በግልጽ ያላሰፈረው ነገር ግን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ይህንኑ ክፍል ጠቅሶ ሲናገር ይህ ሁኔታ የሚፈጸመው መቼ እንደሆነ በመግለጽ ትንቢቱ ፍጻሜ የሚያገኝበትን ወቅት "በመጨረሻው ዘመን" በማለት ለአንባቢዎቹ ሁሉ ያስታውቃል።
8. በአይሁድ ባህል ልብስን መቀደድ የልቅሶና የሃዘን መግለጫ ድርጊት ሲሆን፤ 2ኛ ሳሙ 3፡31 ላይ ዳዊት ምን ያህል በአበኔር ሞት እንዳዘነ ለማሳየት ሕዝቡ ሁሉ ልብሳቸውን እንዲቀዱ ሲያዛቸው እናያለን። እግዚአብሄር በዚህ በኢዩኤል ላይ ልባቸውን እንጂ ልብሳቸውን እንዳይቀዱ ሲናገር፤ ሰዎች ለታይታ ያህል ልብሳቸውን መቀደድ እንደሚችሉ ስለሚያውቅ የልብስ መቀደድ ብቻውን በቂ እንዳልሆነና፤ እውነተኛ ንስሃ በእግዚአብሄር ፊት መግባት ካስፈለገ የልብ መቀደድ እንደሚያስፈልግ ነው የሚናገረው።

# <u>ጥናት ሶስት ኢዩኤል 3፡1-21(ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጌታ እግዚአብሄር ሊያደረግ እየተዘጋጀ ያለው ነገሮች፤ በቁ1 ላይ እንደሚነግረን ለህዝቡ ለይሁዳና ለእስራኤል ምርኮን እንደሚመልስ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ እስራኤልን ባስጨነቁትና ክፉ ባደረጉት አህዛብ ላይ ፍርድን እንደሚያመጣ ነው የምናነበው። እነዚህ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩና እግዚአብሄር ምርኳቸውን ሊመልስላቸው ያሉትን ሰዎች የሚጠራባቸው ሶስት ስሞች፡- አንደኛው ርስቴ የሚል ነው፤ ሁለተኛው ሕዝቤ የሚል ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ እስራኤል የሚል ነው።
2. ይህ በገላ 6፡7 ላይ ሰፍሮ የምናገኘው መመሪያ በኢዩ 3፡4-8 ውስጥ በተግባት ተፈጻሚ ሆኖ የማየው፤ ጢሮስና ሲዶና የተባሉት ከተሞች በእግዚአብሄር ሕዝቦች ላይ ያደረሱባቸውን በደሎች ምንም እንኳን ምን ያህል ዓመታት እንዳለፉ ባናውቅም እግዚአብሄር ጊዜውን ጠብቆ በተለይም ቁ7ትን ስንመለከት እነርሱ ያደረጉባቸውን ነገሮች በእነርሱ ላይ መልሶ በማምጣት የዘሩትን ራሱን ሲያሳጭዳቸው ነው የምመለከተው።
3. ማንኛውም የጦር መሪ ቢሆን ሊገጥመው ያለው ጠላቱ ለጦርነቱ ዝግጅት እንዲያደርግ ጊዜ መስጠትና ማስጠንቀቂያን መላክ የማይታሰብ ነገር ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ግን እግዚአብሄር ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ቢኖር በቀጥታ ይህንኑ ነው፤ ይህንን የሚያደርግበት ምክንያትም ጠላት ቢዘጋጅም ሆነ ባይዘጋጅ ለእግዚአብሄር ምንም ዓይነት ለውጥ ስለማያመጣ ነው። አህዛብ ከእግዚአብሄር ጋራ ለመዋጋት ምንም ዓይነት ዝግጅት ቢያደርጉ፤ ከቁ12-13 እንደምንረዳው እግዚአብሄር ሰብስቦ ለፍርድ እንደሚያቆማቸው ነው የምናነበው።
4. "የእግዚአብሄር ቀን" በሚባለው ቀን ብዙ የሚሆኑ ነገሮች እንዳሉ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብንረዳም እንኳን፤ ይህ ክፍል ያሰፈረልን ግን፡- ይህ ቀን ፀሐይና ጨረቃ የሚጨልሙበት ቀን ነው፤ ከዋክብትም በዚህ ቀን አያበሩም፣ እግዚአብሄር ከጽዮን ጮሆ የሚናገርበት ቀን ነው፣ እግዚአብሄር ከኢየሩሳሌም ያንጎደጉዳል፣ በዚህ ቀን ሰማይና ምድርም እንኳን ይናወጣሉ። ለፍጥረት ሁሉ ይህ ቀን አስፈሪ እንደሆነ ግልጽ ቢሆንም እንኳን ቁ16 ላይ እንደምናነበው ከሆነ የእግዚአብሄር ሕዝቦች በመባል የሚታወቁት ግን እንዳይፈሩና እንዳይደነግጡ እግዚአብሄር እርሱ ራሱ መሸሸጊያና መጠጊያ እንደሚሆናቸው ተነግሮናል።
5. ኢዩኤል ከላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ እግዚአብሄር በአህዛብ ላይ ሊያደርግ ያለውንና ሕዝቡን እስራኤልን በምን መንገድ እንደሚታደግ፣ በምድሪቱ ላይ የሚመጣውን አስከፊ ጊዜ ከዘረዘረ በኋላ ነው በዚህ ቁጥር መክፈቻ ላይ "ከዚያም" ማለቱ ይህ ሁሉ ከተከናወነ በኋላ ማለቱ ነው። በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር ራሱን እንደ አምላካቸው አድርጎ ነው የሚያስተዋውቀው፤ ይህም የሆነው ምናልባትም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለማድረግ ከእረኛነቱና ከአባትነቱ ይልቅ አምላክነቱን መናገር ትክክለኛ ስለሆነ ይመስለኛል።
6. ከእግዚአብሄር ወገን ሆነው በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ምድር የሚኖሩት የዚህን ጊዜ ቶሎ መድረስ የሚያስመኟቸው ሃሳቦች ብዬ የማምነው፡- በኢዩ 1፡16 ላይ እንደምናነበው ደስታ ጠፍቶበት ከነበረው ከእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ቁ18 እንደሚናገረው የምንጭ መፍለቂያ መሆኑ አንዱ ሲሆን፤ እግዚአብሄር እንደቀድሞው ደግሞ ጽዮንን መኖሪያው እንደሚሆን መናገሩ ወቅቱን ከሚያስናፍቋቸው ነገሮች መሃል እንደሆኑ አስባለሁ። የእግዚአብሄር ጠላቶች ያንን ቀን እንዳይናፍቁ የሚሆኑበት ምክንያት፤ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሄር በቁ21 ላይ የህዝቡን ደም እንደሚበቀል መናገሩ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር በደለኛ የሆነውን በምልጃም ሆነ በምንም መንገድ ንጹህ ስለማያደርገው ነው።
7. ከ1-3 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በአህዛብ ላይ እንደሚፈርድ ሲናገር ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ስላደረጓቸው ነገሮች እንደሆነ እንመለከታለን፤ ካደረጉባቸውም ነገሮች መሃል ጥቂቶቹ የሚዘረዝራቸው ነገሮች መሃል፤ ምድሩን እንደከፋፈሉት፣ ሕዝቡንም በህዝቦች መሃል እንደበታተኗቸው፣ ወንዶቹን ልጆች የዝሙት አዳሪዎች እንዳደረጉና የመሳሰሉትን ግፎች መፈጸማቸውን ነው የሚቀጣው።